# በረከተ-መርገም

ጥበብ ተሰርቶ አየን_ወይን ላይ ተስሎ
ጥጉብ ሆነች የሚል_ ትግራይ እናት በቅሎ።
* * * * * *

ወያኔን አየነው _ ደመና ላይ ታዝሎ
መቸም ከኔ በላይ _ጌታ የለም ብሎ።
* * * * * *

ሰማዩን አየነው _ አርግዞ ደመና
ዕራስ ላይ ተቀምጠው _ዳሽንና ጉና።
* * * *

ጎንደሮች ለትግሬ_ ልጃቸውን ዳሩ
ወልቃይት ፀገዴን _ማጫ እያስቆጠሩ።
* * * *

ፀለምት ገዳም ገባ_ ዋልድባ ጠቅሎ
ይህአባ መባሉ _ፅድቅ ያስገኛል ብሎ።
* * * *

መተማ አብደራፊ___ቋራም ሆድ ሲብሰው
ሱዳን ተሰደደ _ መሬቱም እንደ ሰው።
* * * *

አዳኝ አገር ጫቆ _ አርማጭሆ ቋራ
ወልቃይት ፀገዴ_ አጅሬ ጃኖራ
ማይለሃም ማይፀምሪ _ተርናሻና ብራ
አምባራስ ደረስጌ _ ሰሜን ጃን አሞራ
ሀሙሲት በለሳ _ደጎማና ደራ
አለፋ ጣቁሳ _ደንቢያና ፎገራ

ጉና ደብረታቦር _ ኢየሱስ ተራራ
በረከተ መርገም_ ታቅፎ በክንዱ
አምጦ እማይወልደው_ ልጅ ይዟል በሆዱ።

* * * *

መድሎ ዘረኝነት _ መከራና ስቃይ
በብድር ይሰጣል _ይፋ ባደባባይ
ይብላኝ ላበዳሪ _ ዕዳውን ተከፋይ።
* * * *

ከንግዲህ ተነስቶ _ ሰው አይሆንም ብሎ
አማራን ወያኔ _ ጥሎታል ዘልዝሎ
መሞቱንስ ይሙት_ ቢገደል ክፉኛ
ዘር ሙቶ ይቀራል?_ አፈር ላይ ከተኛ?

የካቲት 2001
abraham beyenne